ትልቁ ጂሃድ የሚባለው ግፈኛ ባለስልጣን ዘንድ ፍትሀዊ ንግግርን መናገር ነው።

ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "ትልቁ ጂሃድ የሚባለው ግፈኛ ባለስልጣን ዘንድ ፍትሀዊ ንግግርን መናገር ነው።"
[لغيره حسن] [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በአላህ መንገድ ከሚደረጉ የጂሃድ አይነቶች መካከል ጠቃሚውና ትልቁ እውነተኛና ፍትሀዊ ንግግርን ግፈኛና በደለኛ ባለስልጣን ወይም መሪ ዘንድ መናገር እንደሆነ ገለፁ። ምክንያቱም በመልካም የማዘዝና ከመጥፎ የመከልከል ትልቁን መገለጫ ነውና የሰራው። ይህም በንግግርም፣ በጽሑፍም፣ በተግባርም ይሁን ከዚህ ውጪ ባሉ ጥቅም የሚገኝበትና ጉዳት የሚወገድበት በሆነ በማንኛውም መልኩ ሊፈፀም ይችላል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3045